# ኢትዮጵያችን

*“አሀ አሕ ኢትዮጵያችን” ጋዜጣዊ መግለጫ* መጋቢት 05 ቀን 2009 ዓ.ም. (March 14, 2017)

## ሕዝባዊ ናዳ ሊውጠው የሚገባ አገዛዝ



የሰው ልጆች ከአሞራና ውሻ ጋር የሚበላ ሲሻሙ

ቅዳሜ መጋቢት 2 ቀን 2009 ዓ.ም. ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ በአዲስ አበባ ደቡብ ምዕራብ ክፍል በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ በተለምዶ “ቆሼ ሠፈር” እየተባለ በሚጠራው ቆሻሻ ማጠራቀሚያ በደረሰው የመሬት መናድ አሳዛኝ አደጋ፣ የሕዝብ እልቂት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን ከ“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” እንገልጻለን።

የወያኔ አገዛዝ ሕዝባችንን ለኀሊና በሚዘገንን አኳያ በረሃብ እየቀጣ መሆኑ በተደጋጋሚ የተገለፀ ጉዳይ ነው። በመዲናችን አዲስ አበባ ህብረተሰቡ የዕለት ጉርሱን እንዳያገኝ በተለያየ መልኩ ይቀጣል። በየቤቱ ያለውን ረሃብተኛ ቤት ይቁጠረው። በቀን አንዴ ለመመገብ ያለውን እሩጫ የሚፈጋው ያውቀዋል። ወያኔ በተለይ ከ1997 ዓ.ም. የምርጫ ክስረት በኋላ የ“አዲስ አበባን ሕዝብ እንቀጣዋለን” እንዳለው አንዱ ጅራፉ ረሃብ ነው። ሆን ተብሎ እጅግ ባሻቀበው የኑሮ ውድነት ሕዝቡ እንዲገላታ ተደርጓል። የወያኔንና የባለፀጎችን ትርፍራፊ ከቆሻሻ መጣያ እንዲለቅሙ የተገደዱ ቤተሰቦች ቁጥር ቀላል አይደለም። በሀገራችን በተለምዶ ስለ እግዚሃብሔር ብሎ ለመጣ የኔብጤ እንኳ ትርፍራፊ አይሰጥም። ዛሬ ግና ትርፍራፊን በጉርሻ የሚነግዱ ተበራክተርዋል። ከጉርሻ ሽያጭ ያመለጠው ደግሞ ከሚጣልበት ቆሻሻ ይለቀማል። ዛሬ በዘመነ ወያኔ የሰው ልጆች ከአሞራና ውሻ ጋር የሚበላ ሲሻሙ ማየት እውን እድገት ነውን? እውን ሕፃናትና ወጣቶች የሚላስ ሚቀመስ ለማግኘት ቁሻሻ ውስጥ ሲተራመሱ ማየት ለአንድ መንግስት የኅሊና እርካታ ሊሰጥ ይገባልን? አዎ! ለወያኔ ዓይነት በሀገር፣ በሕዝብ፣ በሰንደቅ ዓላማችን፣ በታሪካችን፣ በክብራችን ለመጣ ግፈኛ አገዛዝ እንደ “ድል ፍሬ” ያስፈነድቃል፤ ያስጨፍራል።

ለአለፉት 25 ዓመታት በዝርፊያ ላይ የተሰማራው ወያኔ አዲስ አበባን ከተማ ወደ ቆሻሻነት ዝቅ ካደረጋት ዓመታት ተቆጥሯል። በየመንደሩ ለጤናና ለኑሮ በአስከፊ መልኩ ያሉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎችና አስታኮ ያሉ መጸዳጃዎች ለዚህ በቂ ምስክር ናቸው። የሚያነሳቸው አጥተው በየቦታው የተከማቹ የቆሻሻ ገንዳዎች ለጤና ጠንቅነታቸው ተዘንግቶ ዛሬ ዋናው የምግብ መፈለጊያ፣ ረሃብ ማስታገሻ ሆነዋል። በከተማዋ ከየአካባቢውና ሆቴል ቤቶች የሚጋዘውን ቆሻሻ የሚከማችበት ቦታ ደግሞ ይባሱን በነዋሪነት ደረጃ፣ በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ምንጭ መሆኑን ስናይ እውን ይህ "ዘመነ እርግማን" ወያኔን አስታኮ እየጋለበን ለመሆኑ መረዳት አያዳግትም።

ወያኔ በአዲስ አበባ ነዋሪ ላይ በቋጠረው ቂም ጥናትና ዕቅድ ሳይኖረው ከየመኖሪያ ቤታቸው እያፈናቀለ ለጎዳና ተዳዳሪነት፣ ለላስቲክና "ጨረታ" ቤት ነዋሪነት ያጋለጣቸው ቤተሰቦች ቁጥር ቀላል አይደለም። "ሲያጨሷት እየጨሰች ያለኝ እመስላለሁ" እንዲሉ ገበናቸውን በድሃ ጎጆአቸው ደብቀው ሕይወትን የሚገፉ ቤተሰቦች ዛሬ በወያኔ ግፍ በየአደባባዩ እየተሰቃዩና እየተንገላቱ ይገኛሉ። የ"ቆሼ ሠፈር" ነዋሪዎች ቤታቸውን ተነጥቀው እንደ ዕቃ ከተወረወሩት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች እጅግ ጥቂቶቹ ናቸው። የዕለት ጉርሳቸውን አጥተው፤ ለማየት አይደለም ለመናገርና ለመጻፍ በሚሰቀጥጥ አኳሃን ማንነታቸውን፣ ስብህናቸውን ወያኔ/ህወሀት ሸጦባቸው ለቁሻሻ ተመጋቢነት አጋልጧቸዋል። በየጊዜው በላያቸው ላይ የሚወረወረው የቆሻሻ ክምር እነሆ! በመቶዎች የሚቆጠሩ ሕጻናትን፣ ወጣቶችን፣ እናቶችንና አባቶችን በሕይወት ቀብሯል።

መጋቢት 2 ቀን 2009 ዓ.ም. በተለምዶ "ቆሼ ሠፈር" በመባል በሚታወቀው ደቡብ ምዕራብ አዲስ አበባ በደረሰው የመሬት መደርመስ ሕይወታቸው ያለፈውና የተጎዱት በትንሹ ከ300 ሰው በላይ እንደሆነ ይገመታል። እነኚህ ወገኖቻችን የወያኔ የግፍ ቅጣት ሰለባዎች መሆናቸውን እናሰምርበታለን። ይህን ቁጥር የአገዛዙ ባለስልጣኖች እጅግ አሳንሰው ለማቅረብ ሞክረዋል። በአካባቢው የነበረውን ነዋሪ ከነቤቱ የቀበረው በዚህ ወያኔ ሰራሽ አደጋ የሞተውና የተጎዳው ሰው ቁጥር ከዚህ እንደሚበልጥ ይገመታል። ማንነታቸው ያልታወቀ እንደ ዕቃ የተወረወሩ የላስቲክና "ጨረታ" ቤት ነዋሪዎች ቁጥር ከዚሁ ይካተታል። በዚህ ቆሻሻ ማከማቻ ስፍራ ረሃብን ለማስታገስ መኖሪያቸው ያደረጉ ወገኖቻችን አገዛዙ በጥይት ብቻ ሳይሆን በረሃብ ናዳ ገዳይ ሥርዓት ለመሆኑ ምስክር ናቸው። ክብራቸውን ሸጠው የመጨረሻው አማራጭ ከተጠራቀመ ቆሻሻ የቀጣይ ሕይወታቸው ማስታገሻ ያደረጉ ወገኖቻችን እልቂት የአገዛዙ ቸልተኝነት ሳይሆን ሆን ተብሎ ከተዘረጉት የግፍ ቅጣቶች አካል አድርገን እንመለከተዋለን። የወያኔ ሕዝብን በረሃብ በመቅጣት ከዕለት ጉርሱ ሌላ እንዳያስብ ለማድረግ የተሸረበ ድርጊት አንዱ አካል ለመሆኑ ተደጋግሞ ተነግሯል። ሕፃናት ከምግብ እጦት የተነሳ ከትምህርት ይልቅ በየመንገዱ ሲለምኑና ለተለያየ የመንገድ ዳር ችርቻሮ ሸያጭ ሲዳረጉ ማየቱ የተለመደና እጅጉን እየተበራከተ ያለ ጉዳይ ለመሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። ከራሳቸው አልፈው ቤተሰብን ለመደጎም ገላቸውን የሚቸረችሩ ሕፃናት እህቶቻችንና ልጆቻችን ቁጥር ቀላል አይደለም። ከሥራ ማጣትና ከረሃብ የተነሳ በየአካባቢው መድረሻና መሄጃ ያጡ ተስፋቸው የተሟጠጠ ወጣቶች ከአገዛዙ አንጻር የ "25 ዓመቱ ስኬታማ" ውጤት ናቸው።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይህን በረሃብ የተቀጣ ሕዝብ የዕለት ገቢው ከቆሻሻ መጣያ የተለቀመ ትርፍራፊ መሆኑን እየተገነዘበ ለማሻሻል አለማሰብ ካለማወቅ ሳይሆን የህወሀት/ኢሕአዴግ የአገዛዝ ፖሊሲ አካል በመሆኑ ተጠያቂነቱ ለዋናው የወያኔ አስኳል ኃይሎች ብቻ ሳይሆን ከባችሁ ለምታጨበጭቡ ሁሉ መሆኑን "አህ አሕ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ልናስገነዝብ እንወዳለን። በሰው ልጆች ረሃብ ለምትሳለቁ፣ ረሃብን መቅጫ ላደረጋችሁ፣ ኅበረተሰባችን እናንት የተፋችሁትን ትርፍራፊ ለቃቃሚ ስታደርጉ ጊዜ አይጠይቀንም ብላችሁ እንዳትሳለቁ። ዛሬ በዘረፋና ሌብነት የታወረ አእምሯችሁ፣ ኅብረተሰቡን የሚበላ ያለህ እንዳሰኛችሁ ሁሉ የፍትህ ያለ! የፍርድ ያለህ! እናንተ ላይ እንደሚያነጣጥር አትጠራጠሩ እንላለን።

ሰሞኑን በኦሮሞና በሶማሌ ነዋሪዎች አዋሳኝ ወረዳዎች እየተከሰተ ላለው ዕልቂት፣ በጋምቤላ አኝዋክ ማኅበረሰብ ላይ ከደቡብ ሱዳን በመጡ የሙርሌ ታጣቂዎች ለተፈጸመው እልቂትና ታፍነው ለተወሰዱ ሕፃናት፣ በአዲስ አበባ "ቆሼ ሠፈር" ለደረሰው ወገኖቻችን እልቂት ጨምሮ በ25 ዓመት የወያኔ አገዛዝ በየአካባቢው የግፍ ሕይወት እንዲገፉ ለተደረገበት ሕዝባችንና በሀገራችን ላይ ለደረሰውና ለሚደርሰው ጥፋት ሁሉ ህወሀት/ወያኔና አጃቢና ከባቢዎቹ ሁሉ በሀገርና ሕዝብ ላይ እንደተሳለቃችሁ፣ እንደፈረዳችሁ የእጃችሁን ምታገኙበት የፍርድ ቀን ለእናንተ እንደሚበረታ መግለጽ እንወዳለን።

"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" በአዲስ አበባ በተለምዶ "ቆሼ ሠፈር" በደረሰው የመሬት መንሸራተት ሕይወታችሁን ላጣችሁ ወገኖች የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እንገልጻለን። አደጋው በአገዛዙ የቸልተኝነት ብቻ ሳይሆን ሆን ተብሎ በተለያየ ጊዜና አካባቢ ከሚደርሱ የጥፋት ዕቅዶች አንዱ አድርገን ስለምንመለከተው ኢትዮጵያንና ሕዝባችንን መጽናናቱንና ብርታቱን ለእናንተ፤ ፍርዱን ለእነሱ እግዚአብሔር ይስጥ እንላለን። ብቸኛው መፍትሄ ልቅሶ ሳይሆን ከ"ሞት አይሻል ሕይወት"ን በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ሀገርንና ሕዝብን ለማዳን ከወያኔ/ኢሕአዴግ በመፋለም ድል ማድረግ መሆኑን በመገንዘብ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ አዛውንት እናት አባቶች፣ ተማሪዎች፣ የክርስትናና የእስልምና ምህመናን፣ ሠራተኛው፣ መምህራን፣ ታክሲ ነጂዎች ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በቁርጠኝነት ይህን "ዘመነ ጥፋት" አገዛዝ ለማስወገድ መነሳሳት ይኖርብናል። የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ እስትንፋስ እስካልጨለመ ድረስ ዕንባና ለቅሶ፣ እስርና ግድያ፣ ረሃብና ሞት፣ ስደትና መንከራተት የማያባራ ዕጣ ፋንታችን ነው። ከወያኔ ለሀገርና

ሕዝብ ሀሳቢነት መጠበቅ ከእባብ እንቁላል እርግብ መጠበቅ ነው። እፍኝ የማይሞላ የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ በመቶ ሚልዮን የሚቆጠር ሕዝብ ማሰቃየቱ ሊያበቃ ይገባል። በወያኔ ናዳ ከመሞት ወያኔን ለመናድ መቁረጥ ይኖርብናል። እየገደሉን ሲስቁ ልናለቅስላቸው አግባብነት የለውም። ሀገራችንና ሕዝባችን ለማዳን ከራሳችን በላይ ማንም ሊመጣ አይችልምና የወያኔ አገዛዝ ማብቃት እንዳለበት፤ ሕዝባዊ ናዳ ሊውጠው እንደሚገባ ማሳየት ይጠበቅብናል።

***ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግን የሚያስፈነጥዝ የግፍ ዕንባ።***



**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**
**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**

መጋቢት 05 ቀን 2009 ዓ.ም. (March 14, 2017)


ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com
ምስለ ገጽ : 1H1H Ethiopiachen